ቀን የካቲት 27 ቀን 1995 ዓ.ም
ቁጥር መ30/ጠ56/13/218

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ለአሠራር ዘዴ ቡድን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ የ10ኛ ክፍል ትምህርት እና በተለያዩ ደረጃዎች የሚሰጡትን የ10+1፣ 10+2 እና 10+3 የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎች ላጠናቀቁ የሚከፈለውን የመነሻ ደመወዝ ስለማሳወቅ፣

ቀድሞ የነበረው የትምህርት ፖሊሲ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ የተሻሻለ በመሆኑ በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ የ10ኛ ክፍል ትምህርት የመሠከለኛ የሙያና ቴክኒክ ሥልጠና በ10+1፣ 10+2 ደረጃና የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዲፕሎማ በ10+3 ደረጃ ለሚያጠናቅቁ ሠልጣኞች የመነሻ ደመወዝ መወሰን አስፈልጓል።

ስለዚህ የትምህርት ሚኒስቴር የሠቲት 21/1995 ዓ.ም በቁጥር 4/1-6149/11667/35 በተጻፈ ደብዳቤ በቀድሞውና በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሱ ስለሚሰጡ ትምህርቶች ባስተላለፈው የአቻ ግምት ማረጋገጫ መሠረት፡-

- ከ1993 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ 10ኛ ክፍል አጠናቆ ሰርተፊኬት ለተቀበለ ብር 325/ ሠስት መቶ ሃያ አምስት ብር/፣
- ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ 10ኛ ክፍል +1 ዓመት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና አጠናቆ የመሠከለኛ ባለሙያ የምስክር ወረቀት ደረጃ 1 ለተቀበለ ብር 381/ ሦስት መቶ ሰማንያ አንድ ብር/፣
- ከ1995 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ 10ኛ ክፍል+2 ዓመት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና አጠናቆ የመሠከለኛ ባለሙያ የምስክር ወረቀት ደረጃ II ለተቀበለ ብር 450/ አራት መቶ ሃምሥ ብር/፣
- ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ 10ኛ ክፍል +3 ዓመት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና አጠናቆ ዲፕሎማ ለተቀበለ ብር 530/ አምስት መቶ ሰላሳ ብር/፣

የመነሻ ደመወዝ የተወሰነ መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር